## ሙሴ ወዳጄ ምነው?

አብዮትን ያህል ዳገት
ቅልበሳን ያህል ቁልቁለት
የአርባ ስንት አመት ፈተና
ደከመህ መሰል ይሁና!

ሙሴ ወዳጄ ምነው?

ግን እኮ ነበር መሃላ
ከድል በመለስ ወደኋላ
ሳንል እስከ ዳር ልንገፋ
ለማን ጥለኸን ትጠፋ?

ሙሴ ወዳጄ ምነው?

ጓዶች ጓዲቶች ያኔ ሲያልፉ
ከግራ ከቀኝ ሲረግፉ
ይድረስ ለታጋይ መልእክታችን
ምን ይል ነበረ ዜማችን

ሙሴ ወዳጄ ምነው

ገና ስንት ሌሎች ይሰዋሉ
በሌላ ታጋይ ይተካሉ
በኒያ ሰማእታት የትግል ፋና
ህዝብ እስኪበቃ ለድሉ

ሙሴ ወዳጄ ምነው?

ህዝብ ተርቧል እንቢ ለእኔ
ህዝብ ተጠምቷል ኑሮ ምኔ
በቃኝ ከሚሉ ኩነኔ
እንቀጥል ነበር ያልነው ያኔ

ሙሴ ወዳጆ ምነው?

ጓዶች ጓዲቶች አለንና
አይቆምም ትግሉ ተፅናና
እንቀጥላለን አሁንም
አንት ምሰሶዋችን ባትኖርም።

ሙሴ ወዳጄ ምነው?

ትግሉ መራር ነው ተባብለን
ላናፈገፍግ ተማምለን
ስንት እየገበርን ተቋቁመን
ከዚያማ ወዲህ ስንት አየን

ሙሴ ወዳጀ ምነው?

አብዮትን ያህል ዳገት
ቅልበሳን ያህል ቁልቁለት
የአርባ ስንት አመት ፈተና
ደከመህ መሰል ይሁና!